# በውይይቱ ሂደት ላይ ሊጣሉ የታሰቡ ደንቃራዎች !

**ኢብሳ ነመራ** 02-09-17

ከሃያ ቀናት በፊት ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ ባቀረበው ግብዣ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ 23 ገደማ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለውይይት ታድመው እንደነበር ይታወሳል። ኢህአዴግ ባቀረበው የውይይት ግብዣ ላይ ማናቸውም ህጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መሳተፍ እንደሚችሉ ማስታወቁም ይታወሳል። በኢህአዴግና ህጋዊ ሆነው በሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ውይይት ለማካሄድ የታሰበው በምርጫ ስነምግባር ደንቡ መሰረት የተቋቋመው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ውስጥ ነው። የምርጫ ስነምግባር ደንቡን ተወያይተውና ተደራድረው በፊርማቸው ያጸደቁ ፓርቲዎች የሚሳተፉበት ይህ ምክር ቤት ባለፈው ዓመት ከጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ጋር ውይይት ባደረገበት ወቅት *በመንግስት/ኢህአዴግና በተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ውይይት እንዲካሄድ* የሚል ሃሳብ ቀርቦ ጠቅላይ ሚኒስትሩም በሃሳቡ ተስማምተው እንደነበረ ይታወሳል። ውይይቱ በምርጫው ህግ ላይ የሚያተኩር እንደሚሆን ተገልጾ ነበር። በተለይ የምርጫ ህጉ የሚፈቅደው የቀላል አብላጫ ድምጽ አሸናፊነት ስርአት፣ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንድ ፓርቲ በብቸኝነት እንዲቆጣጠረው ማድረግ የሚችበትን እድል ስለሚፈጥርና ይህም ባለፉት ሁለት ምርጫዎች በተግባር ስለታየ፣ ምክር ቤቱ የአመለካከት ብዝሃነት የሚስተናገድበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ በህዝብ ተወካዮችና በፌዴሬሽን ምክር ቤቶች የስራ ዘመን መክፈቻ ላይ ባደረጉት የመንግስትን የዓመቱን የስራ ክንውን በሚያመለክተው ንግግራቸው ይህንኑ ጉዳይ አንስተው እንደነበረ ይታወሳል። ፕሬዝዳንቱ በንግግራቸው፤

> **…** *የአገራችንን ዴሞክራሲ ለማጐልበት የተለየ እንቅስቃሴ ይደረጋል። ከዚህ አኳያ አንዱ ቀዳሚ ስራ በገዥው ፓርቲና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በሚደረግ ድርድር የምርጫ ህጋችንን የማሻሻል ጉዳይ ይሆናል። አገራችን የምትመራበት የምርጫ ህግ በብዙ አገሮች እንዳለ የሚሰራበት ቢሆንም፣ ከእኛ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ድምፅ ሊሰማ የሚችልበትን አስተማማኝ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ ከመገኘቱ ጋር የህግ ማሻሻያ ይደረጋል። ስለሆነም፤ የምርጫ ህጋችን የአብላጫ ድምፅና የተመጣጣኝ ውክልና ስርዓቶችን በትክክለኛ ሚዛን ያጣመረና የሁሉም የህብረተሰብ ክፍል ድምፅ የሚሰማባቸው ምክር ቤቶች እንዲኖሩን ለማድረግ በሚያስችል ሁኔታ እንዲስተካከል ይደረጋል። ይህም በፓርቲዎች መካከል በሚካሄድ የሰጥቶ መቀበል መርህ የሚገዛና አገራዊ ጥቅማችንን ማዕከል ባደረገ ግልፅነትን የተላበሰ የድርድር ሂደት የሚፈፀም ይሆናል። ነበር ያሉት፤*

በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ድርድርና ውይይት እንዲካሄድ በማድረግ ረገድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ቀዳሚውን ድርሻ እንደሚይዝ በድጋሚ እንዲታወስ እፈልጋለሁ። እርግጥ የጋራ ምክር ቤቱ አባላት ባመቻቹት እድል የምክር ቤቱ አባል ያልሆኑ ፓርቲዎችም ተጠቃሚ ይሆናሉ። ለዚህ ነው የውይይቱ ጥሪ ማንኛውንም ህጋዊ ሆኖ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀስ ተቃዋሚ ፓርቲ የሚመለከት እንዲሆን የተደረገው፤

በጽሁፉ መግቢያ ላይ እንደተመለከተው፣ ህጋዊ ሆነው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥር 10 ቀን 2009 ዓ/ም በአገራዊ ጉዳይ ላይ ውይይትና ድርድር ማድረግ የሚያስችል ቅድመ ሁኔታ ላይ ተወያይተዋል። የውይይቱን ማብቃት ተከተሎ የኢህአዴግ ጽህፈት ቤት በሰጠው መገለጫ፤ በውይይቱ *መጀመሪያ በአገር ጉዳይ ላይ መወያየት፣ መከራከርና መደራደር አስፈላጊ ነው? ወይስ አይደለም? ኢህአዴግ በተነሳሽነት የጠራው ውይይት አስፈላጊ ነው? ወይስ አይደለም?* በሚሉ ጉዳዮች ላይ ውይይት መደረጉን አመልክቷል። በመቀጠል፤ 1ኛ የስብሰባ ስነ ስርዓቱ ምን መሆን

አለበት? 2ኛ የመድረክ መሪነት እንዴት መካሄድ አለበት? 3ኛ የፕሬስ መግለጫ አሰጣጥ እንዴት መከናወን ይገባዋል? 4ኛ የውይይት ታዛቢ ማን መሆን አለበት? በሚሉ አራት ነጥቦች ላይ ውይይት መደረጉን አስታውቋል። በመጨረሻም እስከ ጥር 25 ባለው ጊዜ ውስጥ በአገር አቀፍ ደረጃ የተመዘገቡና በውይይቱ ላይ የተሳተፉት ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያላቸውን አቋም በሚያስቀጥሉበት ጉዳይ ዙሪያ ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ መግባባት ላይ ተደርሷል።

በዚህ መሰረት፤ በድርድሩ ላይ የሚሳተፉት ፓርቲዎች በእነዚህ የውይይት ስነስርአት ጉዳዮች ላይ አስተያየታቸውን አቅርበዋል። በተለይ ስድስት ፓርቲዎች ማለትም፤ የመላው ኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (መኢአድ)፣ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ)፣ የመላው ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ አንድነት ድርጅት (መኢዴአድ)፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ አንድነት ፓርቲ (ኢብአፓ)፣ የኢትዮጵያ ራዕይ ፓርቲ (ኢራፓ)፣ እና ሰማያዊ ፓርቲ አስተያየታቸውን በጋራ ማቅረባቸውን ሰምተናል። **"የውይይት ስነምግባር አማራጭ ሃሳብ"** በሚል የቀረበው የስድስት ፓርቲዎች የውይይት አካሄድ አስተያየት ይፋ በሆነበት መግለጫ ሌሎች ተቃዋሚ ፓርቲዎችም በጋራ እንዲቆሙ ጥሪ ቀርቧል። መግለጫው *መንግስት እንደከዚህ ቀደሙ ድርድሮችን ለሚዲያ ፍጆታነትና ለጊዜ መግዣነት ከማዋል ተቆጥቦ ከድርድሩ የሚገኘው ውጤት አገርንና ህዝብን እንደሚጠቅም አምኖ ይንቀሳቀስ* ይላል።

የተቀሩት የፖለቲካ ፓርቲዎች በጉዳዩ ላይ በይፋ የተናገሩት ነገር ባይኖርም በውይይቱ ወቅት በተስማሙበት መሰረት እስከ ጥር 25 ቀን 2009 ዓ/ም የውይይት አካሄድ አማራጫቸውን አቅርበዋል ተብሎ ይገመታል።

ስድስቱ ፓርቲዎች *"የውይይት ስነምግባር አማራጭ ሃሳብ"* በሚል ባቀረቡት መግለጫ ላይ እንደጠቀሱት፣ ፓርቲዎች ግንባር እየፈጠሩ በጋራ የውይይት አማራጭ ቢያቀርቡ ተመራጭ ነው። ኢህአዴግን ጨምሮ በውይይቱ ላይ የሚሳተፉ 23 ፓርቲዎች የየራሳቸውን አማራጭ ማቅረባቸው ሁሉንም ወደሚያግባባ አንድ አማራጭ ላይ የመድረሱን ሂደት ውስብስብና ጊዜ የሚወስድ ሊያደርገው ስለሚችል ነው በጋራ አቋም መያዙ የተሻለ የሚሆነው፤ በጋራ አቋም ይዞ መቅረብ ግን እንደግዴታ ሊጣል እንደማይችል መታሰብ አለበት። *የድርድሩ ግብ አገርንና ህዝብን በመጥቀም ላይ ብቻ ያተኮረ ይሁን* የሚለው ማሳሰቢያም ተገቢ ነው። ይህ ማሳሰቢያ ግን ኢህአዴግን ብቻ ሳይሆን በድርድሩ ላይ የሚሳተፉ ሁሉንም የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚመለከት መሆኑ መታወቅ አለበት።

*ያም ሆነ ይህ*፤ ኢህአዴግና ተቀዋሚ ፓርቲዎች በቅርቡ ወደውይይት/ድርድር ይገባሉ ተብሎ ይጠበቃል። ይሁን እንጂ፤ አንዳንድ ፓርቲዎች በመገናኛ ብዙሃን የሚያንጸባርቋቸው አቋሞች በውይይትና በድርድር ከሚደረስበት አገርንና ህዝብን የሚጠቅም የጋራ መግባባት ከሚገኘው ፋይዳ ይልቅ፣ ድርድሩን ራሱን ተገቢ ላልሆነ የፖለቲካ ትርፍ የማዋል ፍላጎት ያለ መሆኑን የሚያመለከቱ ሆነው አግኝቼያቸዋለሁ። ከእነዚህ መካከል መኢአድ፣ ኢዴፓና ሰማያዊ ፓርቲ በመገናኛ ብዙሃን ያቀረቧቸውን እንመልከት።

መኢአድ፣ በኢህአዴግ/መንግስትና የፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ሊደረግ የታሰበውን ውይይት/ድርድር አስመልክቶ ለመገናኛ ብዙሃን በሰጠው መግለጫ፣ *የፖለቲካ እስረኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱና በፖለቲካ ሰበብ የተመሰረተ ክስ እንዲቋረጥ* የሚሉ ጥያቄዎችን ለድርድር እናቀርባለን ብሏል። ሰማያዊ ፓርቲም በተመሳሰይ፤ . . .*በእስር ላይ የሚገኙ ፖለቲከኞች እንዲፈቱ፣ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የታሠሩ ሰዎች በቅድሚያ እንዲለቀቁ* የሚል አቋም ይዞ ወደ ድርድሩ እንደሚገባ አስታውቋል። መኢአድ አሁን በስራ ላይ ያለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳና የፀረ ሽብር አዋጁ ለፓርቲዎች እንቅስቃሴ እንቅፋት በመሆኑ እንዲፈተሽ ወይም እንዲሰረዝ የሚል አቋም ይዞ ለድርድር እንደሚቀርብ አስታውቋል።

እነዚህን የመኢአድና የሰማያዊ ፓርቲ አቋሞች እንመልከታቸው። በቅድሚያ በኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኛ የለም። አንድ ግለሰብ *የፖለቲካ እስረኛ* ሊባል የሚችለው፤ በያዘው፣ በሰላማዊ መንገድ በሚያራምደው፣ በሚደግፈው፣ በሚቃወመውና በሚገልጸው አቋሙ ምክንያት በቁጥጥር ስር ሲውል ብቻ ነው። የአመለካከት፣ አመለካከትን በግልና ከሌሎች ጋር ተደራጅቶ የማራመድ፣ በይፋ የመግለጽ፣ በአመለካካት ለፖለቲካ ስልጣን የመፎካከርና በህዝብ ድምጽ በሚገኝ ውክልና ስልጣን የመረከብ መብትና ነጻነት በኢፌዴሪ ህገመንግስት ተረጋግጧል። መኢአድና ሰማያዊ ፓርቲ የተቋቋሙት፣ ከህገመንግስቱ ጋር የማይጣጣም አቋም ጭምር የሚያራምዱት፣ አቋማቸውን በይፋ የሚገልጹት፣ ለምርጫ የሚፎካከሩት በዚህ ህገመንግስታዊ መብታቸው መሰረት ነው። ሰዎች በአቋማቸውና በአመለካከታቸው የሚታሰሩ ቢሆንማ ቀድሞውኑም የፓርቲዎቹም መስራቾች አይኖሩም ነበር።

ይህ በአመለካከትና በአቋም መታሰር በወታደራዊው ደርግ ወቅት ግን ነበር። ማንም ወታደራዊው ደርግና በኋላ የመሰረተው የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲ (ኢሠፓ) ከሚከተሉት ርዮተ ዓለም የተለየ አመለካከትና አቋም የመያዝ፣ የመግለጽ፣ የማራመድ መብት አልነበረውም። ይህን አድርጎ የተገኘ፣ ድርጊቱን የፈጸመው በሰላማዊ መንገድ ቢሆንም ይታሰራል። ይህ የፖለቲካ እስረኛ ነው።

በኢፌዴሪ የመንግስት ስርአት የፖለቲካ እስረኛ የለም። በፖለቲከኝነት ስራ የሚታወቁ በፍርድ ቤት ቅጣት ተወስኖባቸው፣ አሊያም የፍርድ ሂደታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ እስረኞች ግን አሉ። እነዚህ ግለሰቦች በፍርድ ቤት ክስ የተመሰረተባቸውና በጥፋተኝነት የተፈረደባቸው ግን በፖለቲካ ስራቸው በያዙትና ባራመዱት አቋም ሳይሆን፣ በወንጀል ህጉ ወይም በልዩ ባህሪያቸው ምክንያት በተለየ ህግ የተደነገጉ የወንጀል ድርጊት በመፈጸም ተጠርጥረውና ጥፋተኝነታቸው በማስረጃ ተረጋግጦ ነው። እነዚህ የፖለቲካ እስረኞች አይደሉም። የወንጀል ተጠርጣሪዎችና ታራሚ ወንጀለኞች እንጂ፤ ፖለቲከኛ መሆን ግን በወንጀል ከመጠየቅ አያድንም።

*መኢአድ ያነሳው ሌላው ጉዳይ  አሁን በስራ ላይ ያለው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲነሳና የፀረ ሽብር አዋጁ ለፓርቲዎች እንቅስቃሴ እንቅፋት በመሆኑ እንዲፈተሽ ወይም እንዲሰረዝ የሚል ነው።*

እርግጥ ነው የአስቸኳይ ገዜ አዋጁንም ሆነ የጸረሽብርተኝነት ህጉን በሰላማዊ መንገድ መቃወም በህገመንግስት የተረጋገጠ መብት ነው። አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች በተለይ የጸረሽብርተኝነተ ህጉን ሲቃወሙ የቆዩት በዚህ ህገመንግስታዊ መብታቸው ተጠቅመው ነው። ጉዳዩን የምርጫ መፎካከሪያ አጀንዳ ያደረጉ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ነበሩ። የህዝብ ድምጽ አላስገኘላቸውም እንጂ፤  እነዚህ የጸረሽብርተኝነት ህጉን የሚቃወሙ ፓርቲዎች፣ አገሪቱ በተራ የወንጀል ህግ መከላከልና አጥፊዎችን ለፍርድ ማቅረብ ለማይቻልበት ውስብስብ የሽብር አደጋ ያልተጋለጠች መሆኑን ማሳየት አልቻሉም። ይህን ማድረግ እስካልቻሉ ድረስ የጸረሽብርተኝነት ህጉን በጭፍን መቃወም ለአገርና ለህዝብ ማሰብን አያመለክትም። በመሆኑም በተለይ የአመለካከት ብዝሃነትን ማስተናገድ የሚችል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲኖር በሚያስችል ሁኔታ የህግ ማዕቀፎችን በማስተካከል ላይ እንዲያተኩር የምንጠብቀው የፓርቲዎች ውይይት/ድርድር ላይ የጸረሽብር ህጉ ይነሳ የሚል አጀንዳ በቅድመ ሁኔታነት ይዞ መቅረብ ውይይቱን/ድርድሩን ለማስተጓጎል ከመፈለግ አይለይም።

የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን በተመለከተ ማንኛውም ሰላም ወዳድና ለአገሩ ዘላቂ ሰላምና ልማት የሚያስብ ዜጋ እንደሚረዳው፤ መነሻው ምንም ይሁን ምን ባለፈው ዓመትሙሉና በያዝነው ዓመት መግቢያ ላይ በተቀሰቀሰ ሁከት የአገሪቱን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል ግልጽና ደራሽ አደጋ አጋጥሞ ነበር። መንግስት ይህን አደጋ የመከላከል ህገመንግስታዊ ግዴታ ያለበት መሆኑም ይታወቃል። በተለይ ሁከቱ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ስትራቴጂ ነድፈው የሚንቀሳቀሱ ጠላቶች ከጀርባ ሆነው የሚመሩት በመሆኑ

እጅግ አሳሳቢ አድርጎት ነበር። ይህን ከቦታ ቦታ እየተዛመተ በሰው ህይወትና ንብረት ላይ የከፋ ጉዳት ሲያደርስ የነበረ ሁከት በተለመደው የህግ ማስከበር ስራ መቆጣጣር አልተቻለም። ይህን ተቃዋሚ ፓርቲዎችም ይክዱታል የሚል እምነት የለኝም። እናም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁ ያስፈለገው በአገሪቱ ስትራቴጂካዊ ጠላቶች ይመራ የነበረውን ሁከት መክቶ ሰላምና መረጋጋት ለመመለስ ነው። አዋጁ የአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት በአስተማማኝ ሁኔታ ወደነበረበት እስኪመለስ ብቻ ስራ ላይ የሚቆይ ነው። አዋጁ በፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴም ላይ ሆነ በሌሎች ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ክንውኖች ላይ ምንም ተጽእኖ አላሳደረም። ይህ በተግባር የታየ ነው። *አዋጁ ጊዜውን ሳይጨርስ ይነሳ* የሚለውን አጀንዳ ለድርድር እንደቅድመ ሁኔታ ማስቀመጥ ውይይቱንና ድርድሩን ካለመፈለግ፣ ወይም ከማደናቀፍ ተለይቶ የሚታይ አይመስለኝም።

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲም (ኢዴፓ) እንደድርድር ቅድመሁኔታ የሚያስቀምጣቸው አጀንዳዎች እንዳሉት ተናግሯል። ከእነዚህ መካከል *ወደድርድር ከመግባቱ በፊት፣ ባለፉት 25 ዓመታት በተቃዋሚዎች ላይ ከህገ መንግስቱ ውጪ ለተፈፀመባቸው በደል መንግስት ተጠያቂ መሆኑንና ስህተት መስራቱን አምኖ መቀበል አለበት፤* የሚለው ይገኝበታል። ኢዴፓ የደረሱበትን ህገመንግስታዊ ያልሆኑ በደሎች በማስረጃ አስደግፎ አላቀረበም። ስለዚህ በዝርዝር መሞገት አስቸጋሪ ነው። እስከሚታወቀው ድረስ ግን፤ በተለይ ኢዴፓ እንደፈለገ እንዳይንቀሳቀስ፣ ህዝብ በፓርቲውና በአመራሮቹ ላይ መሰረተ ቢስ ጥላቻ እንዲያድርበት፣ ደጋፊ እንዲያጣ ወዘተ . ትዝብት ሳይፈሩ የሰሩትና በአመዛኙ የተሳካላቸው ቀደም ሲል ወዳጆቹ የነበሩ ፓርቲዎችና ፖለቲከኞች ናቸው። ለኢዴፓ መኮሰስ ውጪያዊ ምክንያት አለ ከተባለ፣ ይህ ውጪያዊ ምክንያት ከፖለቲካ ስነምግባር ውጭ በአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና አመራሮቻቸው በፓርቲው ላይ የተነዛው ከፍተኛ የማጥላላት ዘመቻ ነው። እናም ኢዴፓ ለተደረገበት ጫና ይቅርታ እንዲጠይቁት የሚፈልጋቸው ቡድኖች ወይም ግለሰቦች ካሉ፣ ይቅርታ ጠያቂዎቹ የቀድሞ ወዳጆቹ ከመሆን ሊዘሉ አይገባም። *መንግስት ፓርቲው በዚህ ሁሉ የማጥላላት ዘመቻ ውስጥ የህግ ጥበቃ ተደርጎለት እንዲንቀሳቀስ ከማድረግ ያለፈ ጫና አሳድሮበታል* በሎ ማሰብ ስህተትነቱ ያይላል። እናም ኢዴፓ ይቅርታ የመጠየቅ ፍላጎቱን ወደመንግስት ማዞሩ፤ ለዚያውም ወሳኝ አገራዊ ጉዳይ ላይ ለሚደረግ ውይይት እንደቅድመ ሁኔታ ማስቀመጡ ትዝብት ላይ ይጥለዋል። በሰላማዊ ትግል ፍላጎቱ የተጣለበትን ተስፋ መና እንዳያስቀርም ያሰጋል፤የት ይደርሳል የተባለ ጥጃ ... እንዲሉ !

በአጠቃላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመንግስት/ኢህአዴግ የቀረበውን የውይይት/ድርድር ጥሪ ተቀብለው መቅረባቸው፣ በቀዳሚ ውይይታቸው በተስማሙበት መሰረት የውይይት አካሄድ መመሪያ ላይ አማራጫቸውን ማቅረባቸው የአገሪቱን ዴሞክራሲ አንድ ጋት ፈቀቅ እንደማድረግ ሊወሰድ ይችላል። ይሁን እንጂ፤ የህግ የበላይነትን የሚጻረሩና ነባራዊ ሁኔታውን ያላገናዘቡ አጀንዳዎችን እንደ ውይይት/ድርድር ቅድመሁኔታ ለማስቀመጥ የሚያደርጉት ሙከራ በድርድሩ ሂደት ላይ እንቅፋት ከማስቀመጥ አይለይም። እንደተለመደው ከድርድሩ ከሚገኘው ህዝብንና አገርን የሚጠቅም ውጤት ይልቅ ድርድሩን በማሰናከል፣ መንግስትንና ኢህአዴግን ለችግሩ ተጠያቂ አድርጎ በማቅረብ ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ከማግኘት የትም የማያደርስ የፖለቲካ ስልት የመነጨ እንዳይሆንም ያሰጋል። እናም የውይይቱ ሂደት ስር ሊሻጡ የታሰቡት ደንቃራዎች ይነሱ።